AMHARIC

The Seattle Public Library

ይህ በራሪ ጽሁፍየ ______________________________ ነው።

የኔ ተውላጠ ስም ______________________________ ነው።

# WHAT'S your story?

## 2021 Summer of Learning

ወደ የክረምት ትምህርት (Summer of Learning ) እንኳን በደህና መጡ! ታሪክዎን ለመመርመር፣ ለመፍጠር እና ለማጋራት ከጓደኞችዎ እና ከቤተሰብዎ ጋር ይስሩ! አይነ ህሊናዎን ይጠቀሙ እና በወደዱት በማንኛውም ቅደም ተከተል ይሂዱ። የክረምት ትምህርትን ስለደገፉ የሲያትል የህዝብ ቤተ መጻሕፍት ምግባረ ሰናይ (Seattle Public Library Foundation) እና የእነርሱን እርዳታ ሰጪዎች እናመሰግናለን።

**www.spl.org/SummerOfLearning • #SPLSummer2021**

The Seattle Public Library Foundation · BURKE MUSEUM · The Bureau of Fearless Ideas — Be Kind. Be Creative. Be Fearless. · Powered by Shunpike · African-American Writers' Alliance

@SeattlePublicLibrary @SeattlePublicLibrary @SPLBuzz

# ታሪክዎን ይመርምሩ

ስለ ልጅነት  ጊዜዎ ታላላቆችን ይጠይቁ፤ የሚወዱትን ታሪክ ቤተሰብዎ ውስጥ ላለ ሰው ያንብቡ፤ ወይም ከጓደኞችዎ ጋር አዳዲስ ነገሮችን ያግኙ።





EXPLORE your story

2021 Summer of Learning

@ArtBreakerBT

## ከዋክብት የሚታዩበት ምሽት

ኮከቦቹን መቁጠር ይችላሉ? ወደ ምሽት ሰማይ ይመልከቱ እና የሚችሉትን ያክል ብዙ ኮከቦች ይቁጠሩ። ቁጥሩ ሲጠፋብዎት ወይም ሲደክምዎት፣ እያንዳንዱ ኮከብ እንዴት ለምሽት ሰማዩ ብርሀንን እና ውበትን እንደሚጨምር ያስቡ። ለአለም ውበትን ለመጨመር ማድረግ ወይም ማለት የሚችሉትን ሁለት ወይም ሶስት ነገሮችን ዝርዝር ይጻፉ። ያስታውሱ፣ የድርጊትዎ መጠን ምንም ቢሆን፣ ብርሀን መጨመር እንዲሁም ለውጥ ማምጣት ይችላሉ!

## ጥበብን ማጋራት

አያቶቻችን ለታላላቆቻችን ምክራቸውን በማስተላለፍ ጥበባቸውን ሰጥተውናል። ከእርስዎ የሚበልጡ ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ጥሩ ህይወት መኖር በሚመለከት አንድ የምክር አረፍተ ነገር ይጠይቁ። እዚህ ጋር ምክራቸውን ይጻፉ። አሁን፣ በህይወትዎ ውስጥ ላሉ ታላላቆች አንድ ምክር ይጻፉ፤ እናም ለእነርሱ ያጋሩት።

## የአበቦች ወጎች

በበጋ ወቅት አበቦች የት እንደሚሄዱ እና በጸደይ ለምን እንደሚታዩ አስበው ያውቃሉ?  ስለእነርሱ ታሪክ ይፍጠሩ።

## የተፈጥሮ አይነት ስሜት ይሰማል

በሞቃታማ ቀን፣ ባዶ የሆነውን እግርዎን ሳር ውስጥ ያድርጉ እና ለተወሰኑ ደቂቃዎች አይንዎን ይጨፍኑ፤ ከዚያም አይንዎን እንደገና ከከፈቱ በኋላ ምን እንደተሰማዎት ይጻፉ። ረጋ ብለዋል?ፈርተዋል?ጥንካሬ ተሰምቶታል?

## የእርስዎ ታሪክ

ሲያትል ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከለም ዙሪያ የመጡ ናቸው። የተወሰኑት ለትውልዶች፣ ወይም ለብዙ ሺህ አመታት ያክል እዚሁ ነበሩ። የእርስዎ አያቶች ከየት ናቸው?  በአለም ዙሪያ ፣ ወይም በፓስፊክ ሰሜን ምእራብ ውስጥ በነበረ ጉዞ ቢሆንም፣ አሁን ያሉበት ቦታ ለመድረስ ህዝቦችዎ የተሰደዱባቸውን መንገዶች ዱካ ለመከታተል ከቤተሰብ አባልዎ ጋር ይስሩ።

ስለ ሲያትል ታሪካዊ እና ልዩ ስለሆኑ ሰፈሮች “የሲያትል አካባቢ ታሪክ መፈለጊያ” በሚለው የመፈለጊያ መመሪያ ይረዱ። www.spl.org/SeattleNeighborhoodHistory

# ታሪክዎን ይፍጠሩ

በዚህ ወዳጃችን አይነ ህሊናዎን በመጠቀም የራስዎን አስገራሚ የጥበብ ስራ ይፍጠሩ። ታሪክዎን ለመናገር ማንኛውም የጥበብ አይነት – ዳንስ፣ ግጥም፣ የሸክላ ስራ ጥበብ – በልብዎ የሚሰማዎትን መጠቀም ይችላሉ።

CREATE your story

2021 Summer of Learning

## ልእለ ተፈጥሯዊ

አለምን የተሻለ ቦታ ለማድረግ አንድ ልእለ ተፈጥሯዊ ሀይል መምረጥ ቢችሉ ምን ይመርጣሉ? ምን ይለውጣሉ እና ለምን?

## ውስጣዊ ደስታ

"በውስጤ ደስታ አለ። በውስጤ በጣም በጥልቀት ያለ ደስታ። እንደ ጸሃይ እየበራ እና እየሞቀ የሚሄድ።" Zetta Elliott ፣ ደራሲ
በውስጥዎ ያለውን ደስታ ይሳሉ ወይም ይዘርዝሩ። ደስታ የሚሰጥዎትን ሰዎች፣ ቦታዎች፣ ነገሮች እና ህልሞችን ያካትቱ። ይጠቅልሉት እና በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ ይውሰዱት።



@_AXSM

## እኔ

በዚህ ክፍት ቦታ ላይ "እኔ" በሚል ግጥም ጻፍ።

እኔ: ______________________________
*(የቀኑ የሚወዱት ሰአት)*

እኔ: ______________________________
*(የሚኖሩበት ማህበረሰብ)*

እኔ: ______________________________
*(የሚወዱት እንስሳ እና ለምን)*

እኔ: ______________________________
*(አሁን ማየት የሚችሉት የሚወዱት ነገር)*

እኔ: ______________________________
*(ያነበቡት የሚወዱት መጽሃፍ)*

# ታሪክዎን ያጋሩ

ታሪክን ለመፍጠር ብዙ መንገዶች አሉ – ቃላት፣ ስእሎች፣ ቀለም፣ ዳንስ እና ሌሎችም አሉ። ስለዚህ ይዝናኑ እና ታሪክዎን ለቤተሰብዎ፣ ጓደኞችዎ እና ጎረቤቶችዎ ያጋሩ!

SHARE your story

2021 Summer of Learning



## ሩዝ ምርጥ ነው!

ሁሉም ሰው ሩዝ ይወዳል! በአለም ዙሪያ በጣም ታዋቂ ከሆኑ ምግቦች መከከል አንዱ ነው። ሁሉም ባህል – ሁሉም ቤተሰብ – የራሱ የሆነ ልዩ ማሰሮዎች፣ የምግብ አሰራር ዘዴዎች እና የጣእሞች እና የቅመማ ቅመም ስብስቦች ያሉት ይመስላል። በህይወትዎ ውስጥ ካሉ ምግብ አብሳዮች ውስጥ አንዱን ይጠይቁ: ሩዝን እንዴት ነው የሚሰሩት እና የሚበሉት? ፈጣን? ቢጫ? ነጭ ሽንኩርት? ግሩም መአዛ ያለው ሐረግ? ቅቤ የተቀባ? ባስማቲ? የጫካ? ያገኙትን ይሳሉ እና ይጻፉ እናም የምግብ አሰራር ዘዴዎችን ለማወዳደር ከቤተሰብዎ ውጪ ላለ ጓደኛ ያጋሩ!

## የመጫወቻ መሬት 2000

ምርጥ የመጫወቻ ሜዳ መገንባት ቢችሉ፣ ምን ሊመስል ይችላል? ከጓደኞችዎ ጋር ይገናኙ፤ የሚያልሙትን የመጫወቻ ሜዳ ንድፍ ያውጡ እና ይሳሉ፤ ከዚያም እርስ በእርስ ሀሳቦቻችሁን አጋሩ።

@Maese.Art.By.Eileen.Jimenez

## እናመሰግናለን፤ ወዳጃችን

ለምርጥ ጓደኛዎ ወይም ለሚወዱት ሰው ደብዳቤ ይጻፉ እና ለምን የእርስዎ ምርጥ ጓደኛ ወይም የሚወዱት ሰው እንደሆነ ይንገሯቸው።

Burkeን ይጎብኙ! አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ እና ሙዚየሙ የሚችለውን አቅም ለመቆጣጠር ለሁሉም የበርክ ሙዚየም ጎብኚዎች- የበርክ አባላት፣ የ ዋሺንግተን ዩንቨርሲቲ (UW (University of Washington)) ካርድ ያዦች እና ሶስት (3) እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆችን ጨምሮ - ቅድሚያ የተያዙ በጊዜ የተወሰኑ ቲኬቶች ያስፈልጋሉ። ቲኬቶችን ለማስያዝ በርክ ሙዚየምን ከመጎብኘትዎ በፊት እባክዎ burkevis@uw.edu ላይ ኢሜይል በማድረግ ወይም 206-616-8616 ላይ ደውለው ያነጋግሩን። በሚጎበኙበት ቀን፣ ቲኬቶችዎን፣ የእርስዎን የክረምት ትምህርት ልጥፍ እና በቡድንዎ ውስጥ ላለ እያንዳንዱ ሰው የፊት መሸፈኛዎችን እባክዎ ይዘው ይምጡ።ከጁላይ 1 እስከ ዲሴ. 31፣ 2021 ለሁለት አዋቂዎች እና ለአራት ህጻናት ነጻ ቅበላ አለ። ይህ ስጦታ ከሌላ ማንኛውም ቅናሽ ጋር አይጣመርም ወይም መርሀግብር ላላቸው የቡድን ፕሮግራሞች አይሆንም።